የመጀመሪያ እንክብካቤ ብዙውን ጊዜ ለጤና አገልግሎት እንደ 'የፊት በር' ተደርጎ ይቆጠራል፣ ለታካሚዎች በማህበረሰባቸው ውስጥ የጤና ጥበቃ ምክር፣ ሕክምና እና አስተዳደር ይሰጣል።

የመጀመሪያ እንክብካቤ የሚከተሉትን ያጠቃልላል:

የማህበረሰብ ፋርማሲስት
የጥርስ ሐኪም
ኦፕቶሜትሪስት
የጂፒ እንግዳ ተቀባይ
የጂፒ ነርሶች
የፊዚዮቴራፒ ባለሙያ
የአእምሮ ጤና አገናኝ መኮንን

አስቸኳይ የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ማዕከል
እያንዳንዱ የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ቡድን አባል በተለያዩ መስኮች ሙያ እና ችሎታ አለው፣ ትክክለኛውን ድጋፍ፣ ከትክክለኛው የጤና ባለሙያ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ለማግኘት ይረዳዎታል።

በአካባቢዎ የ NHS የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ አገልግሎት ለማግኘት የሚከተለውን ድረገጽ ይጎብኙ cavuhb.nhs.wales/primary-care-services ወይም የሚከተለውን QR ኮድ ስካን ያድርጉ

Primary Choice leaflet AMHARIC 3-24

ትክክለኛውን ሰው፣ በትክክለኛው ቦታ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በማየት፣ ለጤና አገልግሎት የሚያስፈልግዎን ነገሮች በተገቢው መንገድ ማግኘት ይችላሉ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ማግኘት የሚገባዎት ከሁሉ የተሻለው ሰው የትኛው ቡድን አባል እንደሆነ እርግጠኛ ካልሆኑ እባክዎን የሚከተለውን ድረገጽ ይጎብኙ cavuhb.nhs.wales/primary-care-services.

እንዲሁም ደግሞ በአካባቢዎ የሚገኘውን የ NHS የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ አገልግሎት ለማግኘት የሚከተለውን የፍለጋ መንገዶችን መጠቀም ይችላሉ

**#WeArePrimaryCare**

## NHS 111 ዌልስ

ስለ ምልክቶችዎ እና ምን ዓይነት ድጋፍ እንደሚያስፈልግዎት እርግጠኛ ካልሆኑ፣ NHS 111 ዌልስን በኢንተርኔት መጎብኘት ወይም በሞባይል ወይም ከቤት ስልክ በነፃ 111 መደወል ይችላሉ።

cardiffandvaleuhb @CV_UHB

# PrimaryChoice

## የእርስዎ የመጀመሪያ እንክብካቤ ቡድን

አብዛኛውን ጊዜ የአንደኛ ደረጃ እንክብካቤ ቡድን በመባል የሚታወቀው የማኅበረሰቡ የጤና ጥበቃ ቡድን በማኅበረሰባችሁ ውስጥ ለጤና አገልግሎት የሚያስፈልጉ ፍላጎቶችን ለማሟላት የመጀመሪያው ሕክምና ነው።ሕክምና ነው።

GIG CYMRU NHS WALES
Bwrdd Iechyd Prifysgol Caerdydd a'r Fro
Cardiff and Vale University Health Board



## የማህበረሰብ ፋርማሲስት



በአካባቢህ ያለው ፋርማሲስት፣ መድኃኒቶችን ከመስጠት የበለጠ ተጨማሪ ሞያ አለው። ጥቃቅን በሽታዎችንና መድሃኒቶችን በተመለከተም ምክር መስጠት ይችላሉ።

አንዳንድ የማህበረሰብ ፋርማሲስቶች ለተለመዱ በሽታዎች የ NHS ሕክምና በነፃ መስጠትና መድኃኒቶችን ማዘዝ ይችላሉ።

## የጥርስ ሐኪም



የጥርስ ሐኪም የጥርስ ሕመም፣ የድድ ሕመም ወይም የደም መፍሰስ፣ አስቸጋሪ የሆነ መጨረሻ የሚበቅል የመንጋጋ ጥርስ፣ የጥርስ ሕመም ወይም ሌላ ዓይነት የፊት ሕመም ካለብዎት ሊረዳዎት ይችላል።

## ኦፕቶሜትሪስት



ሃይስትሪት ኦፕቲሽያንስ በመባል የሚታወቁ የአይን ሓኪሞች ለዓይን ጤንነት የሚያስፈልጉ ምክሮችንና ድጋፍ መስጠት ይችላሉ፤ ለምሳሌ የማየት ችሎታዎ፣ የዓይን ሕመምዎ ወይም ጉዳት ያሉ ችግሮችን በተመለከተ።

## የእርስዎ ጂፒ ሕክምና



ጂፒዎን ሲያነጋግሩ በመጀመሪያ ከአንድ እንግዳ ተቀባይ ጋር ይነጋገራሉ። የእርስዎን ፍላጎቶች ለመገምገም እና ለመጀመሪያ ጊዜ ትክክለኛውን የጤና ባለሙያ ለማግኘት እንዲረዳዎት ሚስጥራዊ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ስልጠና ይሰጣቸዋል።

በጂፒዎ ውስጥ ከሁሉ የተሻለውን ምክርና ሕክምና ለመስጠት በተለያዩ መስኮች የተሰማሩ የጤና ባለሞያዎች ቡድን አለ።

## አጠቃላይ ነርስ



ቁስልን ለማከም፣ የወሊድ መከላከያ ምክርና ምርመራ ለማድረግ፣ ለክትባት፣ የደም ግፊት ክትትል ለማድረግና እንደ አስምና የስኳር በሽታ ያሉ ሥር የሰደዱ በሽታዎችን ለመከለስ ወደ አጠቃላይ የሕክምና ነርስህ ይሂዱ።

## የፊዚዮቴራፒ ባለሙያ



አንድ የፊዚዮቴራፒ ባለሙያ የመገጣጠሚያ ወይም የጡንቻ ሕመም ካለብዎት ምክርና ሕክምና ሊሰጥዎት ይችላል።

## የአእምሮ ጤና አገናኝ መኮንን



የአእምሮ ጤና ግንኙነት ሰራተኞች ከጂፒ ሕክምና ጋር አብሮ በመስራት፣ ታካሚዎች የአእምሮ ጤና ፍላጎታቸውን ለማሟላት ይሰራሉ።

## አስቸኳይ የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ማዕከል



አንድ የጂፒ እንግዳ ተቀባይ ወደ አጣዳፊ የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ማዕከል ሪፈር ሊያደርግዎት ይችላሉ።

እነዚህ ማዕከሎች አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ አጣዳፊ እንክብካቤ ማግኘት እንዲችሉ፣ የጂፒ ሕክምናን ለመደገፍ ተጨማሪ እርዳታ አስተዋውቀዋል።

## ጂፒ



የእርስዎ ጂፒ ለተለያዩ ሁኔታዎች ምክር እና ሕክምና ሊሰጥ ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ፣ ለበሽታ በቀላሉ ሊያጠቃቸው የሚችሉ፣ ውስብስብና በጣም ከባድ ሕመም ያላቸው ታካሚዎች ይሆናሉ።